ሰላም! ይህ መልእክት ህጻናት ላይ የሚከሰት ትኩሳት ርዕሰ ጉዳይን የተመለከተ ነው። ትኩሳት ካጋጠመዎት እና ልጅዎ ወደ ዶክተር መሄድ ካስፈለገው ምን ማድረግ እንደሚችሉ በተመለከተ ፍንጮች እሰጥዎታለሁ።

አንድ ህጻን ልጅ በትኩሳት የሚያዘው የሰውነቱ ሙቀት መጠን 38.5 ዲግሪ ሴልሺየስ ወይም ከዚያ በላይ ሲሆን ነው። እድሜያቸው ከ3 ወራት በታች ለሆኑ ህጻናት የትኩሳት መነሻ የሰውነት ሙቀት መጠን 38 ዲግሪ ሴልሺየስ ነው። ህጻኑ ትኩሳት ሲይዘው ጉንጮቹ ይቀላሉ እንዲሁም ግንባሩ ያተኩሳል። በተጨማሪም በአዘብዛኛው የአፍንጫ ፈሳሹ ይበዛል ወይም ሌሎች ምልክቶችን ያሳያል። ሆኖም ትኩሳት አብዛኛውን ጊዜ አደገኛ አይደለም። ትኩሳት ሰውነታችንን ጤናማ እንዲሆን ይረዳዋል።

**ልጅዎን በትኩሳት ሲያዝ የሚከተሉትን 5 ፍንጮች በማድረግ ሊረዱት ይችላሉ፡**

1. ለልጅዎ የሚጠጣው በቂ ውሀ እና ሻይ ይስጡት። አዲስ ለተወለዱ ህጻናት ከሆነ የጡት ወተት ወይም ፎርሙላ ወተት ይስጧቸው።
2. ልጅዎን በቂ እንቅልፍ እንዲተኛ ያድርጉት።
3. ልጅዎን ስስ ልብስ ብቻ ያልብሱት። ሰውነቱን በወፍራም ልብስ አይሸፍኑት።
4. ለትኩሳት ለህጻናት የሚሰጡ ልዩ መድሀኒቶች አሉ። ለልጅዎ የትኞቹ መድሀኒቶች ጥሩ እንደሆኑ ፋርማሲ ይጠይቁ።
5. ለልጅዎ ከፍተኛ ትኩረት ይስጡት። ለምሳሌ፡ ለልጅዎ የሆነ ጽሁፍ ሊያነቡለት ይችላሉ።

**ልጅዎን ወደ ዶክተር መውሰድ ያለብዎ ስለመሆን አለመሆኑ እርግጠኛ አይደሉም? አንድ ህጻን ልጅ በሚከተሉት 8 ሁኔታዎች ወቅት ወደ ዶክተር መሄድ ያስፈልገዋል፡**

1. ህጻኑን ትኩሳት ከያዘው እና ዕድሜው ከ3 ወራት በታች ከሆነ።
2. ትኩሳቱ ከ4 ቀናት በኋላም ካልተሻለው።
3. ትኩሳቱ በመድሀኒት ሊቀንስለት ካልቻለ።
4. ህጻኑ በጣም የሚዳከም ከሆነ። ህጻኑ እራሱን ከሳተ እና ህጻኑን ማንቃት ከባድ ከሆነ።
5. ህጻኑ ፈሳሽ የማይጠጣና ዳይፐሩ ላይ የሽንት ምልክት የማያሳይ ከሆነ።
6. ህጻኑ በጭንቅላቱ ወደፊት ማጎንበስ የማይችል ከሆነ ወይም ጭንቅላቱን ሲነካ የሚያመው ከሆነ።
7. ህጻኑ ሰውነቱ ላይ ቀያይ ነጠብጣቦች ያሉት ሽፍታ የሚወጣበት ከሆነ። እነዚህን ሁኔታዎች መፍታት ካልተቻለ እና መፈታት የሚያስፈልጋቸው ከሆነ።
8. ህጻኑ በትኩሳት ምክንያት ሰውነቱን ማዘዝ የሚያቅተው ከሆነ። ጡንቻዎቹ ከተንቀጠቀቀጡ፣ እራሱን የሚስት ወይም አይኖቹ የሚንቀዋለሉ ከሆነ።

ምን ማድረግ እንዳለብዎ አያውቁም? የወላጅ ምክር ማዕከል ወይም የህጻናት ህክምና ቢሮ ተገኝተው ይጠይቁ። ሁሉንም አድራሻዎች እና የስልክ ቁጥሮች ከ www.meinkindistkrank.ch ላይ ማግኘት ይችላሉ

ለእርስዎና ለልጅዎ መልካሙን ሁሉ እመኝላችኋለሁ!